የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ–ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4[th] Year No. 59
ADDIS ABABA - 7[th] July, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፯/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ከስዊስ ኮንፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ........ ገጽ ፰፻፵፮

CONTENTS

Proclamation No. 127/1998
The Investments Promotion and Reciprocal Protection Agreement with the Government of the Swiss Confederation Ratification Proclamation ........ page 846

**አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፯/፲፱፻፺**

**ከስዊስ ኮንፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በስዊስ ኮንፌዴሬሽን መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት ጥቅምት ፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በየሕጎቻቸው መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን ተዋዋዮቹ ሀገሮች አንዱ ለሌላው ሲያሳውቁ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለጸ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

**PROCLAMATION NO. 127/1998**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE INVESTMENTS PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE SWISS CONFEDERATION**

WHEREAS, an Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Swiss Confederation, on the promotion and reciprocal protection of investments was signed in Addis Ababa on the 16[th] day of October, 1997;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the day when both contracting parties have notified each other that their legal requirements for the entry into force of international agreements have been fulfilled;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 7[th] day of July, 1998;

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከስዊስ ኮንፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፯/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በስዊስ ኮንፌዴሬሽን መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት ጥቅምት ፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል ።

፫· <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Investments Promotion and Reciprocal Protection Agreement with the Government of the Swiss Confederation Ratification Proclamation No. 127/1998."

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on the Promotion and Reciprocal Protection of Investments signed in Addis Ababa on the 16th day of October, 1997 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Swiss Confederation is ratified.

3. *Power of the Ethiopian Investment Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 7th day of July, 1998.

Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE